# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ

## የታክስ ከፋይ ምዝገባ እና ስረዛ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 4/2012

ህዳር 2012 ዓ/ም

ባህር ዳር

# የታክስ ከፋይ ምዝገባ እና ስረዛ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 4/2012

## 1) አውጪው ባለስልጣን

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 135 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2010 አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 2) አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የታክስ ከፋይ ምዝገባ እና ስረዛ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 4/2012**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3) ትርጓሜ

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሀረግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"የታክስ ከፋይ ምዝገባ"** ማለት በታክስ ህግ መሰረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበትን ሰው በጸደቀው ቅጽ መሰረት በመመዝገብ የምስክር ወረቀት መስጠት ነው፡፡
2) **"የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር"** ማለት በታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ሰው ለታክስ ህጎች ዓላማ ሲባል ተለይቶ የሚታወቅበት በገቢዎች ቢሮ የሚሰጥ የተለየ መለያ ቁጥር ሲሆን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎችን ለይቶ ለማወቅ የሚሰጠውን ቁጥር ይጨምራል፡፡
3) **"ተቀጽላ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር"** ማለት ከአንድ በላይ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ውስጥ በንግድ ሥራ ወይም ቤት በማከራየት ገቢ ለሚያገኝ ግለሰብ ወይም ድርጅት በስሙ ከተመዘገበው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በኋላ ወይም በፊት የሚቀመጥ ተቀጽላ ቁጥር ወይም ፊደል ወይም ስረዝ ነው፡፡
4) **"የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ"** ማለት በንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን የሚሰጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም በየጊዜው የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ነው፡፡